# የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስና ጥበቃው በኢትዮጵያ፣ በኢትዮጵያዊነትና በሰንደቅ ዓላማ ላይ ነው።

*ከአስተዋይ በቀለ*

ልብ በል ኢትዮጵያዊ !!

ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነትና ሰንደቅ ዓላማችን መለኰታዊ ኃይል ያለው፣ የሕያው እግዚአብሔር በረከት፣ ረድኤት፣ ይቅርታው፣ ምሕረቱ፣ ቸርነቱ፣ ፀጋው፣ ተስፋው፣ ጥበቃውና ድል- ነሽነቱ የተሞላበት ዘላለማዊ ቅዱስ ሕልውና ነው።

በዚህ መለኰታዊና ዘላለማዊ ሕልውና ፊት በጠላትነትና በአፍራሽነት የቆሙ የቅርብም- የሩቅም፣ የውስጥም- የውጭም፣ የዛሬውም- የነገውም ተጻራሪ ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጣና በጥበቃው ኃይሉ ይቀሰፋሉ።

በፈጣሪ ቁጣ ፈርኦንና ግብፆች በልዩ ልዩ መቅሰፍት እንደተመቱ ሁሉ የኢትዮጵያ፣ የኢትዮጵያዊነትና የሰንደቅ ዓላማ ጠላቶችንም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር አምላካችን እንደ እነርሱ ይፈጃቸዋል።

ንጉሥ ሰለሞን ሞገስን፣ ጥበብን፣ ዕውቀትንና፣ ማስተዋልን ከእግዚአብሔር የተሰጠው ንጉሥ ነበር። ይህ ንጉሥ እሥራኤል ላይ ያያት ፀሐይ ፀንታ ታበራለች ብሎ ሲፈነጥዝ፣ ያቺ ፀሐይ ግን ወደ ደቡብ ሄዳ ኢትዮጵያ ላይ የበለጠ ፈክታና ደምቃ ለዘላለም በአገራችን ላይ ስታበራ ሲያያት ያኔ ለካስ እግዚአብሔር አምላካችን ይበልጥ የሚወዳት ኢትዮጵያን ነው ብሎ በሃዘን ተገነዘበ።

ትክክል ነው። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይወዳታል። ኢትዮጵያ የፈጣሪያችን ቅዱስ መንፈስና ፍፁም ፍቅር ያደረባት፣ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ያቀፈች፣ መላእክት የሚወጡባትና የሚወርዱባት፣ አምላክ በታላቅ ኃይሉና ጽንዕት በሆኑት መለኰታዊ እጆቹ የሚጠብቃት ንጽሕትና ቅድስት አገር ናት።

ኢትዮጵያ የሕይወት፣ የቦታና የጊዜ መፍለቂያ እናት የሆነች ዘመን የማይቆጠርላት ዘላለማዊ ሕውልና ያላት አልፋ ኦሜጋ አገር ናት።

ጉዶች፣ እርጉሞች፣ ሐሰተኞች፣ ጠማሞች፣ ቅሌታሞች፣ ኅጠኞች፣ ከፉዎች፣ ዓረመኔዎች፣ መሰሪዎች፣ ባንዳዎች፣ ከሃዲዎች፣ የሥልጣን ጥመኞችና ምድረ-እርኩሳን ግን፤

ኢትዮጵያ አገራችንን በኮንፈረንስ ጠረጴዛ በእርሳስ ተስላ የተፈጠረች የመቶ ዓመት እድሜ ብቻ ያላት ክልል አድርገው ኢትዮጵያዊነትን አቃልለውና ባንዲራዋን አርክሰው ያቀርባሉ።

ኢትዮጵያዊ ስማ !

ይኸን ተንኰል ስትሰማ በማይሆን ክርክር አትጠመድ፣ አትብሸቅ፣ አትቆጣ፣ ኢትዮጵያዊ ኩራትህንና ብሔርዊ ክብርህን ጠብቀህ፣ አንገትህን ቀና አድርገህ እየሳቅህ በሳቅህ ፌዝ ትግል ብቻ ውድቅ አድርገው። ያኔ፣ በእኔ ይሁንብህ ታይቶ እንደሚጠፋ ጢስ ይጠፋሉ።

እግዚአብሔር የበቀል አምላክ ነው። ኢትዮጵያን ይበቀልላታል። በኢትዮጵያዊነት ያላመኑትንም ፈፅሞ ይፈጃቸዋል። ሰንደቅ ዓላማ የደፈሩትንም ድል ነስቶ በመብረቅ እሳት አቃጥሎ አመድ ያረጋቸዋል።

አይዞህ ኢትዮጵያዊ !

በርታ !! እግዚአብሔር አምላክህ የፖለቲካ ትዕቢተኞችንና ጠላቶችህን አጥምዶ የቁጣ እጁን ዘርግቶ ያጠፋልሃል። የአገርህን የኢትዮጵያን መንገድና እድገት ያስተካክልልሃል። ኢትዮጵያዊነትህንም በድል- ነሽነት ያረጋግጥልሃል። ሰንደቅ ዓላማህ ከፍ ብሎ ደምቆ ሠምሮና ፀንቶ በመለኮታዊ ኃይል ለዘላለም ይውለበለብልሃል። በዚህ ደስ ይበልህ። አንተ በበኩልህ ደግሞ፣ ለእግዚአብሔር አምላክህ ጩኸት ማሰማትህን፣ ልመናህንና ጸሎትህን ሳታሰልስ ቀጥል።

*ምንጊዜም !*

*ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነትና ሰንደቅዓላማ*

*እናሸንፋለን !!*